# በክርስቶስ ማደግ

## በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት

**ለቡድን መሪው የተሰጠ መመሪያ፡-**
በሉቃስ ወንጌል ጴጥሮስ፣ያዕቆብና ዮሐንስ እንዲከተሉት ጌታ ኢየሱስ ጠራቸው። ኢየሱስን መከተል የሚለው የሕይወት ጉዞ ከዚህ ይጀምራል። እነዚህ ሰዎች ብዙ ነገር መማር እንደሚያስፈልጋቸው ልጆች ናቸው። ከእነርሱ ውስጥ ታላቅ ማን እንደሆነ ይከራከሩ ነበር። በመንግስተ ሰማይ ከኢየሱስ ጎን ማን እንደሚቀመጥ ይከራከሩ ነበር። እንዲሁም ይቆጡ ነበር፤ በሌሎችም ላይ እሳትን ለማውረድ ይፈልጉ ነበር። ይህ ልክ የልጅነት ባህሪ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች አዲስ ነገር ይማሩ ነበር፤ ወደ ጌታም ፍጹም ሙላት ያድጉ ነበር። በኢየሱስ ስቅለት ጊዜ ኢየሱስን የካደው ጴጥሮስ በጣም በሚገርም ሁኔታ በሐዋሪያ ሥራ መጽሐፍ ስናይ ለብዙ ሺ ሰዎች ወንጌልን በድፍረት ሲሰብክ እናያለን።

ሰዎች ዳግመኛ ሲወለዱ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሕፃናት ይሆናሉ። አንዳንድ ሰዎች በቤተክርስቲያን ዕድሜ ቢያስቆጥሩም በመንፈሳዊ ሕይወት ሕፃናት ይሆናሉ። እኛ በመንፈሳዊ ሕይወት እንድናድግ እግዚአብሔር ይፈልጋል። እኛ ሥራውን እንድንሠራ እግዚአብሔር ሊያሰለጥነን ይፈልጋል።

ይህ ‹‹በክርስቶስ ማደግ›› ለሚለው ርዕስ ሦስት ተከታታይ ታሪኮች አሉት። ከእነዚህም የመጀመሪያው ታሪክ ‹‹በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት›› ነው። ሁለተኛው ታሪክ ‹‹በክርስቶስ ማደግ›› ነው። ሦስተኛው ታሪክ ‹‹ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ማደግ›› የሚል ነው። ለእያንዳንዱ ታሪክ የቃል ጥናት ክፍሎች፣መሠረታዊ ጥያቄዎችና ተከታታይ ትምህርቶች አሉት። እነዚህ ትምህርቶች አማኞች በጌታ እንዲያድጉና እለት እለት ከጌታ ጋር በመጓዝ ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት እንዲያድጉ የሚረዱ ናቸው።

**ለመሪው፡- እነዚህን መመሪያዎች አንብብ፡**

1. ይህ የመጀመሪያው ተከታታይ ታሪክ አዲስ ጌታን በተቀበለ ክርስቲያን ሕይወት ላይ ያተኩራል። ምናልባት ከዚህ በፊት ይህንን ታሪክ ተምረህ ሊሆን ይችላል። አሁን ግን በጌታ ባለህ አዲስ ሕይወት ላይ ትኩረት አድርግ።
2. የታሪኮች ዝርዝር፣የአራት ጥያቄዎች ዝርዝርና የቃል ጥናት ዝርዝር ለእያንዳንዱ የቡድን አባል ተቀምጧል።
3. **እያንዳንዱ የቡድን አባል በየሳምንቱ ታሪኮችን እንዲማር አበረታታ፤ ለውይይትም ራስህን አዘጋጅ።**
4. የመሪውን መመሪያ መሪው ብቻ ነው የሚይዘው። በመሪው መመሪያ ውስጥ ለውይይት የሚረዱ ብዙ ጥያቄዎች አሉ። በመሪው መመሪያ ውስጥ ያሉ አራቱ ጥያቄዎች ተለቅ ብለው ይቀመጣሉ።
5. ታሪኩን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የቡድን መሪዎች ተጨማሪ ጥያቄዎችን ሊያዘጋጁ ይችላሉ። ‹‹ታሪኩን ለመረዳት የሚጠቅመኝ ጥያቄ ምንድነው?›› ‹‹የቡድኑ አባላት በዋናው ነጥብ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ሊረዱ የሚችሉ ጥያቄዎች ምንድናቸው?›› ብለህ ራስህን ጠይቅ።

6. የትምህርቶቹ ቅደም ተከተል፡
   ሀ. የባለፈውን ሳምንት ትምህርት ከልስ፡፡
   ለ. የዛሬውን ትምህርት መግቢያ አንብብ፡፡
   ሐ. ታሪኩን ተናገር፡ ታሪኩን ለመናገር እንዲዘጋጅ ከቡድኑ አባላት ለአንዱ ቀድመህ ልትናገር ትችላለህ፡፡
   መ. የቡድኑ አባላት ታሪኩን እንደገና ይናገራሉ፡፡ የቡድኑ መሪ፡- ‹‹ማን፣ምን፣መቼ›› የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ ያደርጋል፡፡
   ሠ. ታሪኩን አንብብ፡፡
   ረ. የውይይት ጥያቄዎች

**በክርስቶስ ማደግ፡- በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት ትምህርት**

**የቃል ጥናት ክፍሎች፡-**

**መዝ፡51፡10፡-** አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤የቀናውን መንፈስ በውስጤ አድስ፡፡

**2ቆሮ፡5፡17፡-** ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል፡፡

**ገላ፡2፡20፡-** ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው፡፡

**አራቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች**

1. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
2. በዚህ ታሪክ ውስጥ ከክርስቶስ የተነሣ የሰዎች ሕይወትና ምኞት እንዴት ይለወጣል?
3. ስለ እግዚአብሔር ስለ መመስከር ምን ትማራለህ?
4. እግዚአብሔር በዚህ ታሪክ ውስጥ አንተን የሚያስተምረው ምንድነው?

   1. የእርሻውና የዘሩ ምሳሌ፡- ሉቃ፡8፡4-15
   2. የጌርጌሴኖን ርኩስ መንፈስ፡- ማር፡5፡1-20
   3. ኢየሱስና ኒቆዲሞስ፡- ዮሐ፡3፡1-21
   4. የሳምራዊቷ ሴት፡- ዮሐ፡4፡3-42
   5. የአንድነትና የፀሎት ቀን
   6. ሳውል፡- ሐዋ፡9፡1-22
   7. ቀራጩ ዘኬዎስ፡- ሉቃ፡19፡1-10
   8. አላዓዛርና ባለ ጠጋው ሰው፡- ሉቃ፡16፡19-31
   9. በመስቀል ላይ የተሰቀለው ክፉ አድራጊ፡- ሉቃ፡23፡38-43
   10. የራስህን ታሪክ ለቡድንህ አባላት ማካፈል፡- ምስክርነትህን ስጥ::

## <u>ትምህርት፡-1</u>

**<u>በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት፡-</u> <u>የዘሩና የዘሪው ምሳሌ</u>**

**<u>የቃል ጥናት ክፍል፡-</u> መዝ፡51፡10፡-** አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤የቀናውን መንፈስ በውስጤ አድስ።

**<u>ለመሪው፡</u>**- መግቢያውን አንብብ። የጌታ ኢየሱስ ተከታይ (ደቀመዝሙር) የሆንክበትን የመጀመሪያውን ቀን አስብ። በዚያን ጊዜ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶህ የተለማመድከውን ልምምድ ለሌሎች መስክረህ ሊሆን ይችላል። ይህንን ከጌታ ያገኘኸውን ልምምድ ለሌሎች ስትመሰክር አንዳንዱ ደስ ብሎት ሲሰማህ ሌላው ላይሰማህ ይችላል። ዛሬ ኢየሱስ ስለ ዘሩና ስለ ዘሪው ታሪክ ያስተምረናል። ይህ ምሳሌ ነው።ጌታ ኢየሱስ መንፈሳዊ እውነት ለማስተማር በምድር ላይ በየእለቱ ከምንኖረው አኗኗር ምሳሌዎችን ተጠቅሟል። ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል ምን ዓይነት ምላሽ እንደሚሰጡ ይህ ታሪክ ያሳያል።
ሰዎች በዚህ ታሪክ ውስጥ ምን ዓይነት ምላሽ እንደሰጡ በጥንቃቄ አድምጥ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-
ታሪኩን ተናገር፡- ሉቃ፡8፡4-15

ታሪኩን እንደገና ከልስ። ታሪኩን ግልጽ ለማድረግ የውይይት መሪዎች የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች፡-

1. ዘሩ የተዘራባቸውን (የወደቀባቸውን) ቦታዎች ስም ጥራ። በእያንዳንዱ ቦታ ምን ሆነ?
2. በእያንዳንዱ ቦታ ዘሩ ፍሬ የማይሰጥበት ምክንያት ምን ነበር?
3. መልካሙ እርሻ ምን ያህል ፍሬ አፈራ?
4. እያንዳንዱ እርሻ ምን ዓይነት ሰው እንደሚወክል ነው ኢየሱስ የተናገረው?
5. ዘሩ ምንን ይወክላል?

ታሪኩን አንብብ።

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ሰዎች ፍሬ እንዳያፈሩ መንስኤ የሆኑ ነገሮች ምንድናቸው?
2. የእግዚአብሔር ቃል እንደ ዘሩ ምሳሌ ነው። ሁኔታዎች ሊለዋወጡ ይችላሉ። ግን ቃሉ አይለወጥም። የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ስንመስክር ከእኛ የምንጠብቀው ምንድነው? ከሚሰሙን ሰዎችስ?
3. የመሰከርነው ቃል ፍሬ ባያፈራ መጨነቅ አለብን?
4. ቃሉን በሰማው ሰው ሕይወት ጥሩ ፍሬ እንዲያፈራ መንስኤ የሚሆነው ምንድነው?
5. የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ከመመስከርህ በፊት የሚሰሙ ሰዎች ምን ዓይነት ምላሽ እንደሚሰጡ ታስባለህ? ይህን ማወቅ ወይም አለማወቅህ በምትሰጠው ምስክርነት ላይ እንዴት ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል? ጥሩ ምላሽ ይሰጣሉ ብለን ለምናስባቸው ሰዎች ብቻ መመስከር አለብን?
6. ስለ መመስከር የተማርነው ምንድነው?

7. ዳግመኛ ስለ መወለድ የተማርከው ምንድነው?
8. ስለ እግዚአብሔር የተማርከው ምንድነው?
9. ዛሬ እግዚአብሔር አንተን የሚያስተምርህ ምንድነው?
10. በዚህ ሳምንት ለማን ትመሰክራለህ?
11. በሚቀጥለው ሳምንት ወንጌልን ለመመስከር እግዚአብሔር ዕድል እንዲሰጥህ ፀለይ፡፡

## ትምህርት-2

**በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት፡- የጌርጌሴኖን ርኩስ መንፈስ፡- ማር፡5፡1-20**

**የቃል ጥናት ክፍል፡- መዝ፡51፡10፡-** አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤የቀናውን መንፈስ በውስጤ አድስ፡፡

**ለመሪው፡-** እኛ በአጋንንት ላይ ስላለው የክርስቶስ ሃይል ላይ አይደለም ትኩረት የምናደርገው፡፡ ትኩረት የምናደርገው ሕይወቱ በተለወጠ ሰው ላይ ሲሆን ያ የተለወጠው ሰው እንዴት እንደሚመሰክር ነው፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎቹ ትኩረት የሚያደርጉት በታሪኮቹ ዓላማ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ስለ አጋንንቶች ብዙ በመናገር ጊዜ አታጥፋ፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች፡-**
ስለ ዘሩና ስለ ፍሬው ባለፈው ሳምንት የተማርከው ምንድነው? ፍሬው በዘሩ ብቻ ነበር የተደገፈው? በምንድነው የተደገፈው? በዚህ ሳምንት የተማርከው የዘሩ ታሪክ በሕይወትህ ላይ እንዴት ተጽዕኖ አመጣ?

**መግቢያውን አንብብ፡-** ይህ ታሪክ የተፈጸመው ኢየሱስ የዘሩን ምሳሌ በተናገረበት ቀን ነው፡፡ ኢየሱስ ለተሰበሰበው ሕዝብ ብዙ ምሳሌዎችን ከተናገረ በኋላ ሕዝቡን ትቶ በታንኳ ወደ ማዶ ተሻገረ፡፡ በዚህ ክፍል የምናየው የዘሩንና የእርሻውን ምሳሌ ሳይሆን በእውነተኛው ሰው ሕይወት የሚሆነውን ነገር ነው፡፡ በእውነተኛው ሰው ሕይወት የሚሆነውን ለውጥ ለማየት ታሪኩን በደንብ አድምጥ፡፡

ታሪኩን ተናገር፡- ማር፡5፡1-20

**ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡**
1. ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት የዚህ ሰው ችግር ምን ነበር? እሱ ያደረጋቸውን ነገሮችና ያለፋቸውን ሁኔታዎች ግለጽ፡፡
2. በዚያ ቦታ የነበሩ ሰዎች እሱን ረድተውት ነበር? ምን አደረጉለት?
3. ሰውየው ኢየሱስን ሲያይ ምን አደረገ? ስለ ኢየሱስ ማንነት እንዴት ሊያውቅ ቻለ?
4. ኢየሱስ ምን ብሎ ጠየቀው? ቀጥሎ ምን ሆነ?

5. የእሪያ መንጋ ላይ ምን ሆነ? ሰውየው እርዳታ ባይደርስለት ኖሮ በመጨረሻ ምን እንደሚሆን ነው ይህ የሚያሳየን?
6. ከሰውዬው ውስጥ አጋንንት ከወጡ በኋላ ሰውዬው ምን ይመስል ነበር?
7. ሕዝቡ ለዚህ ምን ምላሽ ሰጡ?

***ታሪኩን አንብብ፡፡***

***<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>***

1. ይህ ታሪክ ከዘሩና ከእርሻው ምሳሌ ጋር እንዴት ይገናኛል? መልካምና መጥፎ እርሻዎች እነማን ነበሩ?
2. በእንደዚህ ዓይነቱ በአጋንንት በታሠረ ሰው ሕይወት ወንጌል እንዴት መልካም እርሻ ሊፈጥር ይችላል? ይህ ምን ያስተምረናል? ምስክርነት ስንሰጥ ከእኛ የሚጠበቀው ምንድነው?
3. ከአጋንንት እሥራት ነፃ የወጣውን ሰው ኢየሱስ ምን እንዲያደርግ አዘዘው? ታሪኩ መነገር ያለበት ነው? ለዚህ ሰው ኢየሱስ ያደረገውን ታሪክ ለሌሎች መናገር ተገቢ ነው?
4. ሕይወታቸው ተለውጦ ኢየሱስን ስለ ሚከተሉ ሰዎች ምን እንማራለን? በእነዚህ ሰዎች ውስጥ ያለው አዲስ መሻት ምንድነው?
5. ይህ ሰው ስለ ኢየሱስ ብዙ አያውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን ስለ ኢየሱስ ለሌሎች ለመናገር ሄደ፡፡ እኛ ምስክርነት ስንሰጥ ማድረግ ስላለብን ነገር ይህ ምን ያስተምረናል?
6. ኢየሱስ ሕዝቡን በባሕር ማዶ ትቶ ወደዚህ ሰው የሄደው ለምንድነው? ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?

## <u>ትምህርት-3</u>

**<u>በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት፡-</u> <u>የኒቆዲሞስ ታሪክ</u>**

***<u>የቃል ጥናት ክፍል</u>፡- መዝ፡51፡10፡-*** አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፤የቀናውን መንፈስ በውስጤ አድስ፡፡

የባለፈውን ሳምንት ታሪክ ከልስ፡፡ የባለፈውን ሳምንት ታሪክ መናገር የሚችል ሰው አለ? ምስክርነት የሰጣችሁ ሰው አለ? ምስክርነት ከሰጣችሁ በኋላ ምን ሆነ?

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ይህ ቀድሞ የሰማነው ታሪክ ነው፡፡ ግን ከዘሪውና ከዘሩ ታሪክ ጋር በማነጻጸር አስበው፡፡ ይህን ታሪክ ስትሰማ ስለ ሚከተለው ጥያቄ አስብ፡- ኒቆዲሞስ ምን ዓይነት እርሻ ነው?

***ታሪኩን ተናገር፡- ዮሐ፡3፡1-21***

የቡድኑ አባላት ታሪኩን እንደገና ለመናገር እንዲሞክሩ ጠይቃቸው፡፡ እያንዳንዱ ሰው ይሳተፍ፡፡

ታሪኩን አንብብ፡፡

**ለውይይቱ መሪዎች የሚጠይቁት ጥያቄ**

1. ከኒቆዲሞስ ታሪክ ውስጥ አስቸጋሪ የሆነው የተሰቀለውን እባብ ታሪክ የሚናገር ክፍል ነው፡፡ ኒቆዲሞስ ስለ ተሰቀለው እባብ ታሪክ ያውቅ ነበር፡፡ ኢየሱስ ከዚህ ታሪክ ምን ለማስተማር እንደፈለገ ማወቅና መረዳት አለብን፡፡ አንተ ይህን ታሪክ ታስታውሳለህ? ምን ሆነ? ታሪኩ በዘኀል፡21፡7-9 ተገልጾአል፡፡ ለብዙ እሥራኤላዊያን መሞት ምክንያት የሆነው ምን ነበር? እግዚአብሔር እባቦችን ለምን ሰደደ? በዓላማ (በእንጨት) ላይ የተሰቀለው ምን ነበር? እባቦቹ እግዚአብሔር በሰዎች ሐጢአት ምክንያት ለፍርድ የላካቸው ነበሩ፡፡ የናሐስ እባብ ያንን ፍርድ የሚያሳይ ነበር፡፡ በዓላማ ላይ የተሰቀለውን እባብ ሰዎች ሲያዩ ምን ይሆኑ ነበር? እባቡ ነበር የሚፈውሳቸው ወይስ በእግዚአብሔር ላይ የነበራው እምነት? ስለ እግዚአብሔር ምን ትማራለህ?
2. ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የሰው ልጅ እንደ እባብ ሊሰቀል እንደሚገባው ነገረው፡፡ ኢየሱስ ‹‹የሰው ልጅ›› የሚለው ማንን ነው? የሰው ልጅ እንዴት ነበር የተሰቀለው? ስለ ሐጢአት ፍርድና ስለ ደህንነት ይህ ምን ያስተምረናል?
3. ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የነገረው እዛው ባለበት ቦታ መልካም ሰው እንዲሆን ነው ወይስ መንገዱን ሙሉ በሙሉ እንዲቀይር? መልሱ፡- አይ የሚል ሲሆን፣---------------------------------------------------- ይገባሃል›› አለው፡፡ ኒቆድሞስም፡- ‹‹ይህን ማድረግ እንዴት ይቻላል? ዳግመኛ ወደ እናት ማህፀን መግባት ይቻላልን?›› አለው፡፡ ኢየሱስ ምን አለው? ኢየሱስ <በእሱ ማመን ዳግመኛ እንደመወለድ ነው> ማለቱ ነው?
4. ስለ ዳግመኛ መወለድ ከዚህ ታሪክ የምትማረው ምንድነው?
5. ከዚህ በታች ባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ዳግመኛ መወለድ የምትማረው ምንድነው? 2ቆሮ፡5፡17፣ ገላ፡2፡20፣ ሕዝ፡36፡25-27
   **ባዶ ቦታውን ሙላ፡** ዳግመኛ የተወለደ ሰው አዲስ------------ስላለው ይለወጣል፡፡
6. የዘሪውንና የዘሩን ምሳሌ አስብ፡፡ ኒቆዲሞስ ምን ዓይነት እርሻ ነበር? ለምን? ኒቆዲሞስ ዳግመኛ ለመወለድ ማሸነፍ የነበረባቸው ችግሮች ምን ነበሩ?
7. እንዴት መመስከር እንዳለብህ ከዚህ የምትማረው ምንድነው? ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የመሰከረው እንዴት ነበር?
8. አንተ ዳግመኛ ተወልደሃል? በመንፈሳዊ ሕይወትህ ልጅ? ጎልማሳ? ወይስ ወላጅ ነህ?
9. እግዚአብሔር ዛሬ አንተን የሚያስተምርህ ምንድነው?

## ትምህርት-4፡

**<u>በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት፡-</u> <u>የሳምራዊቷ ሴት</u>**

**<u>የቃል ጥናት ክፍል፡-</u>2ቆሮ፡5፡17፡-** ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል፡፡

**<u>ክለሳ፡-</u>** ባለፈው ሳምንት የተማርከው ምንድነው? በዚህ ባለው ሳምንት የመሰክርክለት ሰው ማነው? ውጤቱስ ምን ነበር?

**<u>መግቢያ</u>**፡- ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ሊጠመቁ ወደ እሱ መጡ፡፡ አንድ ቀን ኢየሱስ በሰማሪያ ለማለፍ ወሰነ፡፡ አይሁድ የሰማሪያን ሰዎች ስለ ማይወዱ ከሰማሪያ ውጪ እንጂ በሰማሪያ ውስጥ አያልፉም ነበር፡፡ ይህንን ታሪክ ስትሰማ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስብ፡- የሴቷ ሕይወት ኢየሱስን ከማግኘቷ በፊትና በኂላ ምን ይመስል ነበር? ኢየሱስ ለዚህች ሴት ሊናገር እንዴት የተለያዩ መንገዶችን ተጠቀመ? እሷ ስለ ኢየሱስ እንዴት መሰከረች? ውጤቱስ ምን ነበር?

ታሪኩን ተናገር፡ ዮሐ፡4፡3-42
**ማን? መቼ? የት? ምን? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን እንደገና ተናገር፡፡**

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ኢየሱስ ሴቷ በጥሞና እንድትሰማው ምን አላት?
2. እሷ በመጀመሪያ ምን ዓይነት እርሻ ነበረች?
3. ሴቷ ኢየሱስን ከማግኘቷ በፊትና በኂላ ሕይወቷ ምን ይመስል ነበር? ዳግመኛ የተወለደ ልብ ማድረግ የሚፈልገው ምንድነው?
4. ኢየሱስ ለኒቆዲሞስና ለእሷ የተናገረው መንገድ ተመሳሳይ ነበር? ልዩነቱን ተወያይ፡፡
5. ይህች ሴት ስለ ኢየሱስ ሁሉን ነገር አላወቀችም፡፡ ነገር ግን ያወቀችውን ያህል ለሌሎች ተናግራ ሌሎችን ወደ ኢየሱስ አመጣች፡፡ ስለ ኢየሱስ የነገረቻቸው ሰዎች ምን ሆኑ?
6. ስለ ምስክርነት ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?
7. ዛሬ ስለ እግዚአብሔር የተማርከው ምንድነው?
8. ዛሬ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው?

## ትምህርት-5

**<u>የአንድነት የፀሎትና ጊዜ</u>**

በዚህ ሳምንት አንዱ ለአንዱ ይፀልይ፡፡ እያንዳንዱ ሰው የፀሎት ርዕስ በመስጠት በጎኑ ያለው ሰው እንዲፀልይለት ሊያደርግ ይችላል፡፡ የፀሎት ርዕስ እንዳለቀ ወዲያው አንዱ ለአንዱ ይፀልይ፡፡

ከዚያም ስለ ግል ሕይወታችሁ እርስ በርስ ተነጋገሩ። ከቡድኑ አባላት ውስጥ የተወሰኑት ጌታን እንዴት እንደተቀበሉ እንዲናገሩ አድርግ።

## <u>ትምህርት-6</u>

**<u>በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት</u>፡- <u>አሳዳጁ ሳውል ከኢየሱስ ጋር ሲገናኝ</u>**

***<u>የቃል ጥናት ክፍል</u>*****፡-2ቆሮ፡5፡17፡-** ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

***<u>መግቢያ</u>*****፡-** ይህንን ታሪክ በፊት ሰምተህ ሊሆን ይችላል። ዛሬ በሳውል አዲስ ሕይወት ላይ ትኩረት እናደርጋለን። ሕይወቱ የተለወጠበት መንገድ አስገራሚ ነበር። ሳውል ከጌታ ጋር ከመገናኘቱ በፊት አሳዳጅና የክርስቶስ ተቃዋሚ ነበር። ታሪኩ በደማስቆ መንገድ ላይ ይጀምራል። ሳውል በደማስቆ ያሉትን ክርስቲያኖች ሊያሳድድና ሊያሳስር በኢየሩሳሌም ካሉ የአይሁድ መሪዎች ፍቃድ አግኝቶ ነበር።

**ታሪኩን ተናገር፡ ሐዋ፡9፡1-22**
**ታሪኩን እንደገና ተናገር።**

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ሳውል ሐጢአተኛ ነበር? ሳውል በደማስቆ ያሉትን ክርስቲያኖች ሊያሳድድና ሊይዝ ሲመጣ ሐጢአተኛ እንደሆነ ስለ ራሱ ያስብ ነበር?
2. በሕይወትህ አንድ ነገር ትክክል ነው ብለህ አድርገህ ነገር ግን በኋላ ስህተት ሆኖ ያገኘኸው ነገር ምንድው? ሳውል ያደርገው የነበረው ነገር ሁሉ ስህተት እንደሆነ እንዲያውቅ በደማስቆ መንገድ ላይ ሳለ ምን ሆነ?
3. ሳውል ኢየሱስን በአካል ያሳድድ ነበር? ለምንድነው ኢየሱስ ፡- ‹‹አንተ እኔን ታሳድደኛለህ›› ያለው?
4. በታሪኩ ውስጥ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ሳውል እንዴት እንደተለወጠ ግለጽ።
5. በሐናኒያ ላይ ምን ሆነ? እሱ ወደ ሳውል ለመሄድ ደስተኛ ነበር? ሐናኒያ ምስክርነት ለመስጠት እንዴት ከራሱ ጋር ታግሎ ነበር? በሐናኒያ አመለካከት ሳውል ምን ዓይነት እርሻ ነበር? ለአንዳንድ ሰው ለመመስከር ከራስህ ጋር ታግለህ ታውቃለህ?
6. ሳውል ማወቅ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር አልነገረውም። ሐናኒያ በታሪኩ ውስጥ የራሱ ድርሻ እንዲኖረው እግዚአብሔር ተጠቀመው። ይህ ስለ መመስከር ምን ያስተምረናል?
7. ኢየሱስ ሊያሸንፈው የማይችለው እርሻ አለ?
8. ወንጌልን መስማት አለበት የምትለው ሰው አለ?
9. ኢየሱስን ካገኘህ በኋላ ሕይወትህ እንዴት ተለወጠ?
10. ዛሬ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው?

11. ለመሪው፡- ታሪኩን የበለጠ ለመረዳት የምትጠይቀው ተጨማሪ ጥያቄ ምንድነው?

## ትምህርት-7

**በኢየሱስ የተለወጠ ሕይወት፡- ዘኬዎስ**

**የቃል ጥናት ክፍል፡-2ቆሮ፡5፡17፡-** ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል፡፡

**ክለሳ**፡- ባለፈው ሳምንት ከሳውል ታሪክ ምን ተምረሃል?

**መግቢያ**፡- ይህንን ታሪክ ስንናገር ሦስት ነገሮችን ስማ፡፡ 1ኛ. ከኢየሱስ ጋር የተገናኘው ሰው ስም፡፡ 2ኛ. ሕይወቱ መለወጡን ይህ ሰው እንዴት አሳየ? 3ኛ. ስለ ራስህ ሕይወትና ፤ እንዴት ጌታ እንደለወጠህ አስብ፡፡

ታሪኩን ተናገር፡- ሉቃ፡19፡1-10
የታሪኩን እውኔታዎች እንደገና በመከለስ ታሪኩን ተናገር፡፡ የታሪኩ መጀመሪያ ምን ነበር? ከዚያም ምን ሆነ? ማነው የተለወጠው?

ታሪኩን አንብብ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. አብዛኛው ሰው ዘኬዎስን አይወድም ነበር፡፡ ምክንያቱም እርሱ ቀረጥ ሰብሳቢ ነበር፡፡ በሌሎች አመለካከት ዘኬዎስ ምን ዓይነት እርሻ ነበር? ኢየሱስ በዘኬዎስ ላይ የነበረው አመለካከት ምን ነበር? ይህ ስለ መመስከር ምን ያስተምረናል?
2. ዘኬዎስ እንዲለወጥ መንስኤ የሆነው ነገር ምን ነበር?
3. ዘኬዎስ ሕይወቱ መለወጡን ለሌሎች ለማሳየት ያደረገው ነገር ምንድነው?
4. ዳግመኛ ስለ መወለድ ምን እንማራለን? ኢየሱስ ሕይወቱን የለወጠለት ሰው ማድረግ የሚፈልገው ነገር ምንድነው?
5. ጌታ ኢየሱስን አግኝተህ ወደ እውነተኛው ሕይወት ከመጣህ በኋላ ከሕይወትህ የተወገደው ነገር ምንድነው?
6. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
7. ዘኬዎስ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣን ቢሆንም በሰዎች ዘንድ አይወደድም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ወደ ቤቱ ገባ፡፡ ለመንግስት ባለሥልጣናት መልካምን ስለ ማድረግ ከኢየሱስ ድርጊት ምን እንማራለን?
8. ዛሬ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው?

## ትምህርት፡8

**በክርስቶስ የተለወጠ ሕይወት፡- አልዓዛር**

**የቃል ጥናት ክፍል፡-ገላ፡2፡20፡-** ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።

**ክለሳ**፡- ኢየሱስን አግኝተው ሕይወታቸው የተለወጠላቸውን ሰዎች ታሪክ ስንማር ቆይተናል። እነዚህ ታሪኮች የትኞቹ ናቸው?

**መግቢያ፡-** እንዲሁም ስለ ተለያየ እርሻና ስለ ተለያየ ልብ ተምረናል። በዛሬው ታሪክ ስለ ደንዳና ልብ እናያለን። የእነዚህ ሁለቱ ሰዎች ታሪክ በምሳሌ የቀረበ ነው እንጂ በእውነት የሆነ አይደለም። ጌታ ኢየሱስ በመንገዱ ሲሄድ ለደቀመዛሙርትና ለፈሪሳዊያን አለቆች ምሳሌ ይናገር ነበር። እነዚህ ፈሪሳዊያን የአይሁድን ሕግ የሚጠብቁ ስለሆኑ በኢየሱስ ላይ ይቆጡ ነበር፤ኢየሱስ የሚናገረውንም አይቀበሉም ነበር። የዛሬውን ታሪክ አድምጥና የሁለቱ ሰዎች ታሪክ ልዩነት የቱ ጋ እንደሆነ ልብ በል። ፈሪሳዊያን ምን እንደሚያስቡ ገምት።

የባለ ጠጋውን ሰውና የአልዓዛርን ታሪክ ከሉቃ፡16፡19-31 ተናገር።
ታሪኩን እንደገና ተናገር።
ታሪኩን አንብብ።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ባለፉት ሳምንታት የተማርነው ታሪክና የዚህ ታሪክ ልዩነት ምንድነው?
2. የአልዓዛርና የባለ ጠጋው ሰው ልዩነት ምንድነው?
3. ኢየሱስ ማንኛውም ባለ ጠጋ መንግሥተ ሰማይ መግባት አይችልም ማለቱ ነው?
4. ታዲያ ኢየሱስ ይህንን ታሪክ ለምን ተናገረ? ፈሪሳዊያን ምን ያስቡ ነበር?
5. አንዴ ብትሞት ልትቀየር ወይም ሌላ እድል ልታገኝ ትችላለህ? መግንሥተ ሰማይ የምትገባበትን መንገድ በገንዘብ ማግኘት ትችላለህ? አንዴ ለሞቱ ሰዎች እኛ ማድረግ የምንችለው ነገር አለ?
6. አንዳንድ ሰዎች ልክ እንደ ፈሪሳዊያን በምድር ላይ ስኖሩ ከበለጸጉ እግዚአብሔር እየባረካቸው እንደሆነና ሕይወታቸውም ችግር እንደሌለው አድርገው ያስባሉ። ይህ ታሪክ ምን ያስተምረናል?
7. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
8. ለገሃነም እሳት የተዘጋጁትን ሰዎች ሊረዳቸው የሚችል ምንድነው? እኛ ለእነዚህ ሰዎች ምን ማድረግ እንችላለን? ስለ መመስከር ምን እንማራለን? እኛ የምንማረውን ታሪክ ጎረቤቶቻችን ስለ ኢየሱስ እንዲረዱ ለመርዳት እንዴት መጠቀም እንችላለን?
9. ዛሬ እግዚአብሔር የሚያስተምርህ ምንድነው?

## <u>ትምህርት-9</u>

**<u>በመስቀል ላይ የተሰዋ ሕይወት፡</u>**

**<u>የቃል ጥናት ክፍል</u>፡-ገላ፡2፡20፡-** ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።

**<u>ክለሳ</u>**፡- እነዚህ ታሪኮች ሕይወትህን እንዴት እየለወጡ ናቸው?
**<u>መግቢያ፡-</u>** ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞት ጣር ላይ ነበር። ሁለት ወንበዴዎች በግራና በቀኝ ተሰቅለው ነበር። ብዙ ሰዎች ኢየሱስ ራሱን ያድን እንደሆነ ያፌዙበት ነበር። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ታሪኩን ተናገር፡- ሉቃ፡23፡35-43

በመጀመሪያ ምን ሆነ? ቀጥሎ ምን ሆነ? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን ከልስ:: ታሪኩን አንብብ።

**<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>**

1. ከኢየሱስ ግራና ቀኝ የተሰቀሉ ሐጢአተኞች ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ ግለጽ። ከዚህ የተነሣ ስለ ሰው ምን ትማራለህ?
2. አንዱ ክፉ አድራጊ ሌላውን ክፉ አድራጊ በመስቀል ላይ ሳሉ እንደገሰፀው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ስለዚህ ስለ ገሰፀው ክፉ አድራጊ ምን ትማራለህ? ይህ ሌላውን የገሰፀው ክፉ አድራጊ ስለ ራሱ የሚያውቀው ምን ነበር?
3. ይህ ክፉ አድራጊ ስለ ኢየሱስ የሚያውቀው ምን ነበር? ቁ፤43 በጥንቃቄ አንብብና መልሱን መልስ።
4. ለዚህ ለገሰፀው ክፉ አድራጊ ኢየሱስ የገባው ተስፋ ቃል ምን ነበር?
5. ስለ እግዚአብሔር ምን ትማራለህ?
6. ስለ ደህንነት ምን ትማራለህ? ሮሜ፡8፡1-3 አንብብ።
7. ይህ ክፉ አድራጊ ለደህንነቱ የሚጠቅም ሥራ ለመሥራት ዕድል አግኝቶ ነበር?
8. 1ዮሐ፡5፡13 አንብብ። አንተ እንድታውቅ እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድነው? የዘላለም ሕይወት እንዴት ማግኘት እንችላለን?

## <u>ትምህርት፡10</u>

### <u>የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>

በዚህ ጊዜ ሦስቱን የቃል ጥናት ክፍሎችን በቃል ተናገር፡፡

**<u>መግቢያ፡-</u>** ጌታ ኢየሱስን አግኝተው ሕይወታቸው የተለወጠላቸውን ብዙ ሰዎች ታሪክ ተምረን ነበር፡፡ የአንተ ታሪክ ምንድነው ከ3-5 ባሉት ደቂቃዎች ስለ ራስህ ታሪክ ተናገር፡፡ ስትናገር የሚከተሉትን ሀሳቦች በታሪክህ ውስጥ አካትት፡፡

1. ኢየሱስን ከማግኘትህ በፊት የነበረህን ሕይወት በአጭሩ ግለጽ፡፡
2. ስለ ሰማኸው ወንጌልና እንዴት እንዳመንክ ግለጽ፡፡
3. ኢየሱስን ካገኘህ በኂላ ያለህን ሕይወት ምን እንደሚመስል ግለጽ፡፡

አንዱ ለሌላው በመፀለይ ጊዜውን ያሳልፍ፡፡